# የርዕሰ ገዳማት ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም የዝማሬ መዋዕሲት ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት የወፍጮ ኘሮጀክት አጭር የሥራ ሂደት ሪፖርት ቁጥር 3



የርዕሰ ገዳማት ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም

- **የገዳሙ ሥም** - የርዕሰ ገዳማት ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም
- **የሚገኝበት ቦታ** - በደቡብ ጎንደር በጋይንት ወረዳ ዙር አባ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ልዩ ስሙ ሰዓሊ በሚባል መንደር ከአ.አ 691 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከዋናው መንገድ የአንድ ሰዓት የእግር መንገድ በኋላ ይገኛል፡፡
- **የፕሮጀክቱ ሥም** - የርዕሰ ገዳማት ዙር አባ አቡነ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም እና የዝማሬ መዋሲት ማስመስከሪያ ትምህርት ቤት የወፍጮ ኘሮጀክት፡፡
- **የኘሮጀክት ማረጋገጫ** - ከተመሠረተ 1400 አካባቢ እድሜ ያስቆጠረው የርዕሰ ገዳማት ዙር አባ አረጋዊ ጽርሐ አርያም ገዳም የነበረው መሬት በመሬት ላራሹ አዋጅ በሙሉ በመወረሱ ካለ ምንም መተዳደሪያ እንዲቀር ሆኖል ፣ በገዳሙ የነበሩት መነኮሳት እና አገልጋዮች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየቀነሰ ሲመጣ ዛሬ በገዳሙ ሶስት መነኮሳት ብቻ ቀርተዋል ፣በገዳሙ የቅዱስ ያሬድን መቋሚያ ጨምሮ ጥንታዊ የብራና መጽሐፍ ፣አልባሳትና እና ንዋየ ቅድሳት በተጎሳቆሉ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፣ በቅዱስ የሬድ የተመሰረተው የዝማሬ መዋዕሲት ማስመስከሪያ ት/ቤት ተማሪዎች የቀለብ፣ ልብስ እና የመማሪያ መጽሐፍ ችግር አለባቸው፡፡
- **የፕሮጀክቱ ዓላማ** - ብቸኛ የዝማሬ መዋዕሲት ማስመስከሪያ ት/ቤቱ ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲኖረውና እራሱን እንዲችል ማድረግ፣ የገደሙ ጥንታዊ ፣ታሪካዊ ቅርሶች እና ንዋየ ቅድሳት በአግባቡ እንዲጠበቁ ማድረግ፡፡



የአካባቢው ምዕመናን ወፍጮውን ወደ ገዳሙ ሲያዙ

- **ሪፖርቱ የሚያጠቃልለው ጊዜ** - ከግንቦት 2000 እስከ መስከረም 2001 ዓ.ም.
- **የፕሮጀክቱ ጠቅላላ በጀት** - 89,897..50 ብር

  ገቢ የሆነው የገንዘብ መጠን 9,400 **ዶላር** /88,694.00 **ብር**/
- **የፕሮጀክቱን በጀት የሸፈነው አካል** - በአሜሪካ ማዕከል በኩል ከዲሲ ቅ/ሚካኤል ሰ/ቤት፡፡
- **ፕሮጀክቱ ያለበት ሁኔታ** -

  ⇒ ቀደም ሲል ከተከናወኑት የውል ሰነድ የመፈራረም እና ኮሚቴ የማዋቀር ለግንባታ የሚያስፈልጉ የቁሳቁስ አቅርቦት ከማካሄድ እና ግንባታውን ከማስጀመር በተጨማሪ

  ⇒ **የቤቱን ግንባታ የማጠናቀቅ ሥራ ተሰርቷል**

  ⇒ **አንድ ባለ አርባ እና አንድ ባለ ሀምሳ ቋት ወፍጮ እንዲሁም አንድ ባለ 24 ፈረስ ጉልበት የነዳጅ ሞተር እና ለወፍጮ አስፈላጊ የሁኑ ቁሳቁሶች ግዥ ተፈፅሞ ወደ ገዳሙ ተጓጉዟል**

  ⇒ **የወፍጮ ተከላ ሥራ ተከናውኗል**





## የሂሳብ ሪፖርት

ለቁሳቁስ አቅርቦት እና ለሰው ኃይል.................18,931.00 ብር

ለሁለት ወፍጮ እና ሌሎች ቁሳቁስ ግዥ................15,652.18

ለነዳጅ ሞተር ግዥ...................................................16,347.82

ለማጓጓዧ እና ማስተከያ ...........................................7,247.00

ለነዳጅ እና ሌሎች ወጪዎች ..................................3,050.00

ድምር............................................................................**61,228.00**

ለፕሮጀክት ሥራ ማስፈጸሚያ /15% /..................... 9,184.20ብር

**ጠቅላላ የወጭ ድምር......................................70,412.20 ብር**

**ቀሪ በጀት** .............................................18**,281.80 ብር**





በገዳሙ የወፍጮ ተከላ ሲካሄድ

**ማኅበረ ቅዱሳን**
**የማኅበራዊ አገልግሎት እና ልማት ዋና ክፍል**
**የቅዱሳት መካናት ልማትና ተራድዖ ክፍለ**
**አድራሻ:**
ስልክ: 251 11 1234531፣ 0911150478
ፖ.ሳ.ቁ. 80078 አ.አ ኢትዮጵያ
እሜል Gedamat_mk@yahoo.com